**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ.መ.ቁ 239523
ጥቅምት 26 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

አመልካች፡- አቶ ታዬ ደረሰ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጎሣዬ ደረሰ

2. ወ/ሮ ጽጌ ኪዳኔ

መዝገቡ የተቀጠረው ለፍርድ ነው፡፡ በመሆኑም መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ታሕሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 400565 ሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና በመ.ቁ 400565 ሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 405870 ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ኑዛዜ ይፍረስልኝ በሚል የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ አባት፤ ለ2ኛ ተጠሪ ደግሞ ባለቤት የሆኑት አቶ ደረሰ ቱፋ በቀን 06/09/2013 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ የሟች አባቴ የውርስ ንብረት የሆነ በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ 3000 ካ.ሜ የሆነ ሞቴል እና ፊውል ስቴሽን እንዲሁም በአዳማ ከተማ ውስጥ የሚገኝ 486 ካ.ሜ የመኖሪያ ቤት አለው፤ ተጠሪዎች የአባቴን የውርስ ንብረት እንዲያካፍሉኝ ስጠይቅ ሟች አባቴ በቀን 14/02/2014 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረገ ስለመሆኑ ሽማግሌዎች አንብበውልኝ አውቄአለሁ፤ አመልካች የሚደርሰኝ ድርሻ 60.75 ካ.ሜ ነው፤ ኑዛዜው ከ 25 በመቶ በላይ የሚያሳጣኝ እና ከውርስ የሚነቅለኝ በመሆኑ ኑዛዜው እንዲፈርስ እና የ2ኛ ተጠሪ ድርሻ ተነስቶ ከሟች የምንወለደው ወራሾች እኩል እንድንከፋፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ ተደርጓል፤ በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ ሟች በጋራ ያፈሩት ሞቴል እና ፊውል የሚባል የንግድ ድርጅት የለም፤ 3000 ካ.ሜ በሚል የተገለጸው ይህ ቦታ ባዶ ቦታ ስለሆነ እንደንብረት አይገመትም፤ መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ ሟች ለአመልካች ስለተናዘዘለት ከውርስ ነቅሎኛል ማለት አይችልም፤ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ጉድለት የለበትም፤ ስለሆነም አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበት ፍርድ ቤት ሟች በቀን 25/03/2013 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ሊሰረዝ ይገባል ወይስ አይገባም? ኑዛዜው አመልካችን ከውርስ ነቅሎታል ማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? አመልካች ማግኘት ያለበት የውርስ ድርሻ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ ሟች በቀን 25/03/2013 ዓ.ም ባደረገው ኑዛዜ 486 ካ.ሜ ከሆነው መኖሪያ ቤት ድርሻውን 243 ካ.ሜ አመልካችን ጨምሮ አራት ሰዎች እንዲካፈሉ መወሰኑን ከሟች ሐሳብ መረዳት ይቻላል፤ ሟች በሕይወት እያለ ያደረገው ኑዛዜ ተናዛዡ ካለው መብት እና ድርሻ ውስጥ ኑዛዜ ተቀባዩ ምን ያህል ማግኘት እንዳለበት የሚያሳይ እንደሚ አመልካችን ከኑዛዜ ነቅሎታል የሚያስብል አይደለም፤ 3000 ካ.ሜ የሆነ ሞቴል እና ፊውል ድርጅት በሚል የተገለጸውን ይዞታ በሚመለከት በዚህ ቦታ ላይ የተፈራው ንብረት ብሎኬት ብቻ ነው፤ ሟች ይህን ንብረት የኢንቨስትመንት ሐሳብ ስላለ መልማት ይችላል በሚል የተናዘዘ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ የቦታውን ግምት አስመልክቶ የተደረገ ኑዛዜ አይደለም፤ በአጠቃላይ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ወራሾች ንብረቱን በምን ሁኔታ መከፋፈል እንዳለባቸው የተሰጠ አቅጣጫ እንጂ አመልካችን ከውርስ የነቀለ አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ሟች በቀን 25/05/2013 ዓ.ም በአዳማ ከተማ 3000 ካ.ሜ ላይ የሚገኝ ሞቴል እና ፊውል ስቴሽን ድርሻውን 1ኛ ተጠሪ እንዲያገኝ አድርጎ የመኖሪያ ቤቱን ብቻ ለወራሾች እንዲሆን ያደረገው ኑዛዜ የአመልካችን የመውረስ መብት የሚነካ ነው፤ በዚህ ድርጅት ላይ ያለውን የሟችን ድርሻ ወራሾች እኩል እንዲጠቀሙበት በማለት በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በተራቸው ይህን ወሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ለ1ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ተላልፏል የተባለው ሞቴል እና ፊውል ስቴሽን የንግድ ድርጅት 3000 ካ.ሜ ላይ የሚገኝ ሟች በሞተ ጊዜ ኢንቨስት ያልተደረገበት እና ባዶ ቦታ ነው፤ በዚህ ቦታ ላይ ተፈራ የተባለው ግምቱ ብር 700,000 የሆነ የብሎኬት ምርት ሟች ከሞተ በኋላ የተፈራ በመሆኑ የውርስ ሐብት አይሆንም፤ ሟች በቀን 25/5/2013 ዓ.ም ያደረገው ኑዛዜ የኑዛዜ ስጦታ ስለሆነ ተፈጻሚነቱ በኑዛዜው ውስጥ በተደረገው መሠረት ነው፤ ሟች ባደረገው ኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆነው ልጁ አመልካች  ከመኖሪያ ቤቱ የወራሽነት ድርሻውን እንዲያገኝ ተናዟል፤ ሟች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አመልካችን ከኑዛዜ አልነቀለውም፤ ሟች ባደረገው ኑዛዜ ንብረቱን በኑዛዜ ለማስተላለፍ ባለው መብት ያስተላለፈ እና በዚህ ኑዛዜ አመልካችን ያልነቀለ እና ጉዳት ያላደረሰበት በመሆኑ ኑዛዜው  የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት በሥር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካች የወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ለማሻሻል ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ እና ከውርስ በሚነቅለኝ ኑዛዜ ላይ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም በሚል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 400565 መስቀለኛ ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባናቸው ተሰርዟል፡፡

አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ታሕሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተናዛዥ ጦረኝ ወይም አልጦረኝም በሚል ተወላጅን ከውርስ መንቀል ወይም ከ 25 በመቶ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ ከሕግ ውጪ ነው፤ ሟች የንግድ ድርጅቱን በሚመለከት ያደረገው ኑዛዜ አመልካች ከድርጅቱ ማግኘት ያለብኝን የመጠቀም መብት ሙሉ በሙሉ ያሳጣ ነው፤ ማች አድርጎታል የተባለው ኑዛዜ በሽምግልና ዕድሜው እና በሕመም ላይ ሆኖ የተደረገ እና በአራት ምስክሮች ያልተረጋገጠ እና የሕጉን መስፈርቶች የማያሟላ መሆኑን በመግለጽ አቤቱታዬን እንዳሻሽል የጠየቅኩ ቢሆንም ያለ በቂ ምክንያት ታልፎብኛል፤ ስለሆነም እነኚህ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሳይገቡ በወረዳው ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አከራክሪው ኑዛዜ አመልካችን ከውርስ የነቀለ ወይም ሊደርሰው ከሚገባው ድርሻ አንጻር ከ 1/4ኛ በላይ ጉዳት  ያደረሰበት መሆን አለመሆኑን ለመወሰን በኢንቨስትመንት የተወሰደው 3000 ካ.ሜ ይዞታ የሟች ድርሻ ታሳቢ ሊደረግ አይገባም ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪዎች ሠኔ 02 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጡት መልስ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በሙሉ ፈቃደኝነት አልተደረገም የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤት አልተነሳም፣ ተናዛዡ ያደረጉት ኑዛዜ ወራሾችን ብቻ የያዘ ሳይሆን ወራሽ ያልሆኑትንም ያካተተ በመሆኑ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 912 ነው፣ 3000 ካ.ሜ የሆነው ቦታ ንብረት የሌለበት ባዶ ቦታ ነው፣ ተናዛዡ ሲሞት የነበረው መኖሪያ ቤቱ ብቻ ነው፣ በኑዛዜ ውስጥ ድርሻውን ያገኘ ሰው ከውርስ ተነቅያለሁ ማለት አይችልም፣ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ያስቀርባል ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ሟች አቶ ደረሰ ቱፋ በቀን 25/05/2013 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን፣ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ውስጥ በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 375 የሆነ ስፋቱ 486 ካ.ሜ የሆነ ቤት እና በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በስማቸው የተመዘገበ የሞቴል እና ፊውል እስቴሽን ድርጅት እንዳላቸው በመግለጽ በልዩ ሁኔታ ስታመም ያስታመመኝ ብቻውን እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ እናት እና አባት የሆነልኝ ቤተሰብ እያለው እኔን የተለየ እንክብካቤ ያደረገልኝ እና የጦረኝ ስለሆነ እና ይህ ነው የማይባል ውለታ ስለዋለልኝ በስሜ የተመዘገበውን የሞቴል እና ፊውል እስቴሽን ድርጅት ግማሹን ድርሻዬን 1ኛ ተጠሪ በግል እንዲጠቀምበት ተናዝዠለታለሁ፣ መኖሪያ ቤቱን በሚመለከት ግን ድርሻዬን አመልካችን ጨምሮ ስማቸው በኑዛዜው የተገለጹት ወራሾቼ እኩል እንዲከፋፈሉ በሚል በግልጽ ያስቀመጡ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት አጥብቀው የሚከራከሩት ተናዛዥ ጦረኝ ወይም አልጦረኝም በሚል ተወላጅን ከውርስ መንቀል ወይም ከ 25 በመቶ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ ከሕግ ውጪ ነው፣ ሟች የንግድ ድርጅቱን በሚመለከት ያደረገው ኑዛዜ አመልካች ከድርጅቱ ማግኘት ያለብኝ የመጠቀም መብት ሙሉ በሙሉ ያሳጣ ነው በሚል ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 913 የኑዛዜው ቃል የተናዛዡን ተቃራኒ ሐሳብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሐብት አንድ ድርሻን ወይም አንድን ንብረት ሟቹ ለወራሾች መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ሐሳብ በእንግሊዝኛው እንዲህ በሚል ተቀምጧል፡- "An assignment of a portion of succession or of property forming part of such succession made by the testator to one of his heirs shall not be deemed to be a legacy but a mere rule for partition, unless the contrary intention of the testator emerges from the

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

disposition “ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ /legacy/ ወይም ክፍያ ደንብ /Rule of partition/ ሊሆኑ እንደሚችሉ፤ ተናዛዡ ባደረገው ኑዛዜ ግልጽ ምክንያት አስቀምጦ ተቃራኒ ሐሳብ ካልገለጸ በቀር ከውርስ ሐብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾች መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ እንደማያሰኘው፤ ይልቁንም ይህ ዓይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ መሆኑን ነው፡፡

አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /partition/ በመከተል የሚከናወን ሲሆን ኑዛዜው ስጦታን /legacy/ የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 942 ጀምሮ ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት በማጣራት /liquidation/ ሥርዓት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ክፍያ ደግሞ ክፍፍልን /partition/ በሚመለከቱና ከአንቀጽ 1060 ጀምሮ ባሉ ደንጋጌዎች መሰረት የሚስተናገድ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ሟች አቶ ደረሰ ቱፋ በቀን 25/05/2013 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ውስጥ በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 375 የሆነ ስፋቱ 486 ካ.ሜ የሆነ ቤት እና በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በስማቸው የተመዘገበ የሞቴል እና ፊውል እስቴሽን ድርጅት እንዳላቸው በመግለጽ በልዩ ሁኔታ ስታመም ያስታመመኝ ብቻውን እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ እናት እና አባት የሆነልኝ ቤተሰብ እያለው እኔን የተለየ እንክብካቤ ያደረገልኝ እና የጦረኝ ስለሆነ እና ይህ ነው የማይባል ውለታ ስለዋለልኝ በስሜ የተመዘገበውን የሞቴል እና ፊውል እስቴሽን ድርጅት ግማሹን ድርሻዬን 1ኛ ተጠሪ በግል እንዲጠቀምበት ተናዝዤለታለሁ፤ መኖሪያ ቤቱን በሚመለከት ግን ድርሻዬን አመልካችን ጨምሮ ስማቸው በኑዛዜው የተገለጹት ወራሾቼ እኩል እንዲከፋፈሉ በሚል በግልጽ ተናዘዋል፡፡ በሌላ በኩል ሟች ባደረጉት በዚህ ኑዛዜ ውስጥ ሕጋዊ ወራሽ ያልሆነ ሰው ጭምር ያካተተ ስለመሆኑ እና አከራካሪ የሆነው 3000 ካ.ሜ ይዞታ ባዶ ቦታ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የክፍፍል ደንብ /partition/ ሳይሆን የኑዛዜ ስጦታ የተደረገላቸው ሰዎች /legacy/ የሚመለከተው የሕግ ክፍል ነው፡፡ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ ከ2ኛ ተጠሪዋ ጋር በጋራ ያፈሩት 3000 ካ.ሜ ከሆነው ይዞታ ውስጥ ያላቸውን 50 በመቶ ድርሻ ለ 1ኛ ተጠሪ የሰጡበትን ምክንያት በግልጽ እስካስቀመጡ እና ከመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል እንዲከፋፈል እስከተናዘዙ ድረስ የሚቹን ሐሳብ ባከበር መንገድ ኑዛዜውን ተፈጻሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል በእጃችን ያለው ጉዳይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ላይ በዝርዝር እንደተገለጸው በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል በፌዴራል ጠቅላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም የሚችለው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለውን ሕግ በመጥቀስ ወይም ሕግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ውሳኔ/ ትዕዛዝ/ ብይን ሆኖ ጉዳዩም ለሕዝብ ጥቅም አገራዊ ፋይዳ ያለው ጉዳይ ከሆነ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ የቀረበው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም በኋላ ታሕሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሚኖረው ይኸው አዋጅ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10/1(ሐ)እና(መ) ላይ ከተቀመጡት መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 400565 ሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና በመ.ቁ 400565 ሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 405870 ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   - ሠኔ 07 ቀን 2015 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !